Ministry of Justice

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአምስተኛ ዓመት ቁጥር ፶፫
አዲስ አበባ ሐምሌ ፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

15th Year No 53
ADDIS ABABA 16th July, 2009

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፮/፪ሺ፩ ዓ.ም

ለፀኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት አዋጅ ... ገጽ ፬፻፯፻፮፫

CONTENTS

Proclamation No. 646/2009

International Development Association Financing Agreement for the Fourth Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation …….Page 4763

አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፮/፪ሺ፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለፀኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፩፻፷፮ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. /አንድ መቶ ስልሣ ስድስት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር./ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፭ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፭፩ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለፀኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፮፻፵፮/፪ሺ፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

PROCLAMATION NO. 646/2009

A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount not exceeding SDR 166,000,000 (one hundred sixty six million Special Drawing Rights) for financing the Fourth Road Sector Development Support Project, was signed in Addis Ababa on the 5th day of June 2009;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Financing Agreement at its session held on the 2nd day of July,2009;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows:

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for the Fourth Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation No. 646/2009".

Ministry of Justice

፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማህበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፭ ቀን ፪ሺ፱ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 4561-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፷፮ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር. /አንድ መቶ ስልሣ ስድስት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር./ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፱ ቀን ፪ሺ፩ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Financing Agreement Credit Number 4561-ET signed in Addis Ababa on the 5th day of June 2009 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of 166,000,000 SDR (one hundred sixty six million Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 16th day of July, 2009

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA